**KINIJIT MN**

## የሚኒሶታ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ

## Kinijit Support Group In Minnesota

የሚኒሶታ ድግፍ ሰጪ ኮሚቴ Jun 27 / 2007 ዓ/ም ባደረግነው ስብሰባ ላይ በአሁኑ ግዜ በቅንጅት ኢንተርናሽናል ላይ ያንጃበበውን የማፈራረስ፣ የመከፋፈል ደባ በሰፊው ከተነጋገርበት በሃላ የሚከተለውን ውሳኔ በአንድ ድምፅ አሳልፈን የአቋማችን መግለጫ አድርገነዋል።

1--ለቅንጅት ኢንተርናሽናል ያለን ድጋፍ ከዚህ በፊት ከያዝነው አቋም ምንም የተቀነሰም ሆነ የተቀየረ እንደሌለው አረጋግጠን ። ያለንን አቋም ሊያስቀይር የሚያስችል ምንም አይነት ድርጊትም ሆነ ተግባር ባለመከናወኑ አሁንም ቢሆን አቋማችን ግልፅና ዲሞክራትክ የሆነውን ቅንጅት ኢንተርናሽናል መደገፍ ነው።

2--ከቃሊቲ የተላኩ በተባሉት ሁለት ሽማግሌዎች አስተባባሪነት ተይዞ የነበረው የእርቅ ድርድር ግልጽነት የጓደለው በመሆኑና የቅንጅት ዋና መሣሪያው ግልጽነት በመሆኑ ተደረገ የተባለውን እርቅ ብንደግፍም ከዛ በሃላ የተከተለውን የራስ ጓራ በማጠናከር የቅንጅት ኢንተርናሽኛልን በእጅ ለማስገባት የሚደረገው ጥረት በቁርጠኝነት እናወግዛለን።

3--ከቅንጅት ኢንተርናሽናል ስምንት(8) አባላት ሁሉት ብቻ በተገኙበት ያውም እርግጠኝነቱ ባልተረጋገጠ ደብዳቤ በመመረኩዝ የተደረገውን አዲስ ምርጫ እንደማንቀበለው በማሳወቅ ትግላችንን ከቀሪዎቹ የኢንተርናሽናል አባላት ጋር በማጠናከር አሁኑም መሪዎቻችንን ለማስፈታትና በሀገራችን በኢትዮጵያ ዲሞክራሲን ለማምጣት የሚደረገው ጥረት በሰፊው እንቀጥላለን።

በዚህ አጋጠሚ የእውነተኛ የኢትዮጵያ ልጆች የሆናችሁና የቅንጅትን ማኒፌስቶ የምተደግፉ ወገኖቻችን በቅንጅት ጥላ ስር በመሰባሰብ ትግላችሁን እንድታጠክሩ መሪያቻችንን ለማስፈታት በሚደረገው ጥረት ላይ እንድትረባረው እንጠይቃለን።

በሚኒሶታ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ